## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

### OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሠላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፹፮
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.86
Addis Ababa 28th Jun, 2024


**ማውጫ**


**ደንብ ቁጥር ፻፸፮/፪ሺ፲፮**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኤግዚቢሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ**

ገፅ…………………………………………… ፫ሺ፯፻፴፪


**CONTENT**


**Regulation no. 176/2024**

**Regulation issued to Re-establish Addis Ababa City Government Exhibition Center Market Enterprise**

Page…………………………………….….3732


## ደንብ ቁጥር ፻፸፮/፪ሺ፲፮

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኤግዚቢሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ

ወቅቱን የሚመጥን የኤግዚቢሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ደርጅት ሆኖ እያለገለ ባለመሆኑ ድርጅቱ የተቋቋመበትን የንግድ ዓላማ እና የሚሳተፍበት አትራፊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በግልጽ አስቀምጦ ውጤታማ አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኤግዚቢሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ደርጅት አደረጃጀትና አሰራር ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን ከወጣው ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፲፮ ጋር ማጣጣም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Regulation no. 176/2024

## Regulation issued to Re-establish Addis Ababa City Government Exhibition Center Market Enterprise

**WHEREAS,** it has become necessary to clearly state the business purpose of the organization and the profitable economic activities in which it participates since it is not being used as an exhibition center and market enterprise that suits the season, , and to establish an effective system;

**WHEREAS,** it is necessary to harmonize the organization and operation of the Exhibition Center and Market Development Department with Regulation No. 159/2016 issued by the Addis Ababa City Administration to determine the conditions under which development organizations are managed;


ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሠን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀጽ ፷፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና አንቀጽ ፺፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኤግዚቢሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ድርጅትን እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፸፮/፪ሺ፲፮ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጉም**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ደንብ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፲፮ ነው፣

፪. "ቦርድ" ማለት በደንቡ መሠረት የሚቋቋም የድርጅቱ አንድ የሥልጣን አካል ነው፣

## ክፍል ሁለት
## ስለድርጅቱ መቋቋምና ዓላማ

**፫. መቋቋም**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኤግዚቢሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ደርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፣

፪. የድርጅቱ ተጠሪነት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለሥልጣን ይሆናል፣

፫ ድርጅቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፲፮ መሠረት ይተዳደራል፡፡



**NOW, THEREFORE,** this regulation is issued by the Cabinet of Addis Ababa City Government in accordance with Sub Article (2) of Article 68 and Sub Article (1) of Article 93 the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 84/2023.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This regulation may be cited as "Regulation issued to Re- Establish Addis Ababa City Government Exhibition Center Market Regulation No. 176/2024''.

**2. Definition**

In this regulation, unless the context otherwise requires:

1. "**Regulation**" shall mean the Regulation issued to Determine, Redefine and Lead the conditions of Public Enterprise of Addis Ababa City Administration Regulation No. 159/2024;
2. "**Board**" shall mean a body of authority of the organization established in accordance with the Regulation;

## PART TWO
## THE ESTABLISHMENT AND OBJECTIVE OF THE ORGANIZATION

**3. Establishment**

1. Addis Ababa City Government Exhibition Center Market Enterprise (hereafter referred to as "Organization") has been re-established as a Public Enterprise by this regulation;
2. The Organization's Accountability will be to the Administration Authority of Government Public Enterprises of the Addis Ababa City Administration;
3. The Organization is administered in accordance with the Regulation issued to Determine, Redefine and Lead the Conditions of Public Enterprise of Addis Ababa City Administration Regulation No. 159/2024.

፬. <u>ዓላማዎች</u>

ድርጅቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. የአስተዳድሩን፣ ብሎም የሀገሪቱን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማጎልበትና ለማስፋፋት የሚረዱ ኤግዚቢሽኖችን፣ ባዛሮችን እና ኩነቶችን ያዘጋጃል፤ ያስተናግዳል፤

፪. የቴክኖሎጂ ውጤቶችን፣ ግኝቶችንና ሞዴሎችን፣ የምርት ናሙናዎችን፣ የታሪክ መረጃዎችን እና የወግና የባህል ውጤቶቸን ለህዝበ እይታ ያቀርባል፤ ያስተዋውቃል፤

፫. የሚመለከተውን የአስተዳደሩ አካል እያስፈቀደ የስፖርትና የመዝናኛ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

፬. ለሲምፖዚየምና ለልዩ ልዩ ስብሰባዎች አገልግሎት ይሰጣል፤

፭. በንግድና ቱሪዝም መረጃ ማዕከልነት ያገለግላል፤

፮. የኤግዚቢሽን ማዕከላትን ያስፋፋል፤

፯. ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ይተምናል ያስከፍላል፤

፰. ዓላማውን ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን፡፡

፭. <u>ድርጅቱ እንዲያቀርብ የሚጠበቅበት የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ</u>

በከተማው ላይ የተለያዩ በጎ አድራጎት ተግባራት ላይ መሳተፍ፡፡

፮. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፯ ቢሊዮን ፫፻፸፩ ሚሊዮን ፩፻፲፰ ሺህ ፪፻፷ (ሰባት ቢሊዮን ሦስት መቶ ሰባ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ አስራ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፯ ቢሊዮን ፪፻፶፭ ሚሊዮን ፫፻፸፪ ሺህ ፭፻፺፰ (ሰባት ቢሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሰባ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ስምንት ብር) በዓይነት እና ፩፻፲፭ሚሊዮን ፯፻፵፭ ሺህ ፮፻፷፪ (አንድ መቶ አስራ አምስት ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ስድሳ ሁለት ብር) በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡

፯. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

4. <u>Objectives</u>

The enterprise shall have the following objectives:-

1. Prepare and stage exibitions and bazars which help to henance and promote the economic sector of the City Governement and ultimetly of the country;
2. Facilitet visites toand advertises, techonological outputs, finding and models, product samples, historical relies, traditional and recreational and cultural artifactes;
3. Shall provides sport and recreational services by obtaineing permission from the concerned body of the City Government to that effect;
4. Provide services for symposium and various meetings ;
5. Serve as information center as business and turism;
6. Expands exhibition centers;
7. Determine and collect charges for the services it provides,
8. Carry out other related activities that help to attain its objectives.

5. <u>Public Service Obligation that the Organization is Expected to Provide</u>

Participate in various charitable activities in the city.

6. <u>Capital</u>

the authorized capital for the Organization is Birr 7,371,118,260.00 (Seven billion three hundred seventy one million one hundred eighteen thousand and two hundred sixty) Birr, of which Birr 7,255,372,598.00 (Seven billion two hundred fifty five million three hundred seventy two thousand five hundred and ninty eight) Birr in kind and Birr 115, 745, 662.00 (One hundred fifteen million seven hundred fourty five thousand six hundred sixty two) Birr was paid in cash.

7. <u>Liability</u>

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

**፰. ዋና መስሪያ ቤቱ**

የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በከተማው ውስጥ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፱. ተቆጣጣሪ ባለስልጣን**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለስልጣን የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

**፲. የድርጅቱ አደረጃጀት**

ድርጅቱ:-

፩. የሥራ አመራር ቦርድ፣

፪. አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፣

፫ ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

**፲፩. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

**፲፪ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

.

**8. Head Office**

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa, and may have branch offices elsewhere in other parts of the country as may be necessary.

**9. Supervisory Authority**

Addis Ababa City Administration Public Enterprise Administration Authority shall be the Enterprise's Supervisory Authority

**10. Organization**

The enterprise shall have:

1. Management Board of the Enterprise;
2. A Chief Executive Officer and Deputy Chief Executive Officers as necessary and;
3. The necessary staff.

**11. Duration of the Organization**

The Enterprise is established for an indefinite period duration.

**12. Effective Date**

This regulation shall enter into force as of this 28th day of June, 2024.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of June 2024.**

**ADANECH ABEBE DESA**

**MAYOR OF ADDIS ABABA**